ክፍል ሦስት

ከሰው የሚያግባባ ዓይነ ጥላ

/ሰው አልባ፣ሕይወት አልባ የሚያደርግ/

የእጮኛሞች፣የባለ ትዳሮች፣የጓደኛሞች ፈተና

በቀሲስ ሄኖክ ወ/ማርያም

ወዳጆቼ በክፍል ሁለት ሴቶችን በተለይ መልከሞችንና ወንዶችን ዓይነ ጥላ እንዴት ባለ የፈተና ስልት ትዳር አልባ በማድረግ ከትዳር ዓለም እንደሚያርቃቸው፣ለትዳር የሚጠይቃቸውን ሰው እንዴት እንደሚመልስባቸው ተመልከተናል። በዚህ በክፍል ሦስት ደግሞ ሰውን ከሰው ስለማያግባባው፣ሰውን ከሰው ስለሚያጣላው፣በመጨረሻም ሕይወት አልባ ስለሚያደርገው ዓይነ ጥላ እንመለከታለን። የአባቶቻችን አምላክ ምስጢሩን ይግለጥልን።

ብዙዎች ‹‹ይህን ያህል በአጋንንት ለምን እፈተናለሁ፣አጋንንትማ በእኔ ላይ ስልጣን የለውም›› ይላሉ። አጋንንት በንስሐ ተወስኖ የማይኖር ሰው ላይ፣በጸሎት ተግቶ የማይኖር ሰው ላይ፣በቅዱስ ቁርባን መለኮታዊ ጸጋ የማይኖር ሰው ላይ በጾም በስግደት ያልበረታ ሰው ላይ ሁሌም አጋንንታዊ የበላይነት አለው። አጋንንት አይዘናጋም፣የተንኮል ሥራውን በአግባቡ ያውቃል። እኛ አንድ ሳምንት ብንጸልይ ለአንድ ወር ጸሎት እንተዋለን። ጸሎታችንም በሥጋዊ ሥራ ምክንያት ‹‹እግዚአብሔር የማያውቀው የለም›› እያልን ጸሎት የማንጸልይ ሰነፎች ነን።

እግዚአብሔር የሚያውቀን ስንጸልይ ነው። እግዚአብሔር መከታ ከለላ የሚሆነን በጸሎት ወደ እርሱ ስንጮህ ነው። ይህንን ባላደረግንበት አግባብ፣አጋንንት የሕይወት ግብግብ ቢገጥመን አይደንቅም። አጋንንት እኛን በተለያየ ነገር በመዋጋት የእግዚአብሔር ሰው እንዳንሆን፣መንፈሳዊ ጸጋዎችን እንዳናገኝ፣በተሰጠን እንዳንጠቀም የማበላሸት እና የማኮላሸት ሥራ ይሠራል። ምክንያቱም አጋንታዊ ጥንታዊ ሥራው ነውና።

ወዳጆቼ አጋንንት እኛን ማሰቃየት፣ሕይወታችንን ማበላሸት በእኛ አልጀመረም፣መተናኮልን በእኛ እየተለማመደ አልኖረም። ይልቁንም በሰማይ ቤት የአዳምና የሔዋንን የሰማይ ሕይወት የማጨለም ልምዱን ይዞ ነው ወደ ምደር መጥቶ በእኛ በአዳምና በሔዋን ልጆች አጋንንታዊ የበቀል መከራውን የሚያሸክመን። ከዚህ ጥንታዊ ክፉ ጠላታችን ጋር ለመዋጋት የፈተና ስልቱንና ተንኮሉን ማወቅ ለእኛ የማንቅያ ደውል ስለሆነ የክፋት ጠባዩን ስናውቅ ነው ለመዋጋት የምንችለው። ተንኮሉን ስናውቅ ነው የሕይወታችንን መሠረታዊ ችግር የምናውቀው። ተንኮሉን ስናውቅ ነው አጋንንትን ከስም በላይ በሆነ የተንኮል ተግባሩን የምናውቀው። ስለ አጋንንት ውግያ ስጽፍላችሁ ገድሉን ሳይሆን ተንኮሉን እንድታውቅ መሆኑን እወቁ። እንግዲህ ይህንን ክፉ የሕይወት ጠላት ይዘን ነው ተዘናግተን የምንኖረው።

ተወዳጆች ሆይ ከዓይነ ጥላ አስከፊ እና መጥፎ ጠባይ አንዱ ሰዎችን ከሰዎች ጋር ያለማግባባት ተንኮሉ ነው። በተለይ ከቤተሰቦቻችን ጋር፣ከትዳር አጋራችን ጋር፣ከሥራ ባልደረባችን ጋር፣ከእጮኛችን ጋር፣ከጓደኛችን ጋር በምክንያት እና ያለ ምክንያት እንዳንግባባ ያደርገናል። ካልተግባባን ደግሞ መስማማት አንችልም። ካልተስማማን ደግሞ አብረን መቀጠል አንችልም። ስለዚህ መራራቅን መለያየትን እንደ መፍትሔ እንወስዳለን። ይህ በውስጣችን አሸምቆ የኖረው ዓይነ ጥላ አንዳንዱን እንኳን ከሰው ከራሱም አያግባባውም። ወዳጆቼ ስንት ሰዎች አለን የራሳችንን ባሕይር የማናውቅ። ስንት አለን ወጥ የሆነ ባሕርይ ሳይሆን እንደ በጋና እንደ ክረምት ለሰው የሚሞቅ እና የሚቀዘቅዝ ያልታወቀ ባሕርይ ያለን።

ዓይነ ጥላው በሰዎች ውስጥ ያለመግባባትን ሴራ የሚሠራው በሁለት መንገድ ነው። አንድኛው ከማኅፀን ወይም ከልጅነታችን በመዋረስ ጠባያችንን በማቃወስ የሚጠቀምብን ሲሆን። ሁለተኛውና የብዙዎቻችን ችግር የሆነው ከጊዜ በኃላ የመጣብን አላስፈላጊ የባሕርይ መገለጫችንን በመጠቀም ነው።

ወዳጆቼ እግዚአብሔር ከሰጠን ጸጋዎች ውስጥ አንዱ የባሕርይ ጸጋ ነው። ይህም ከሰው ተግባብተን ተስማምተን የምንኖርበት ትልቅ ጸጋ ነው። ሰው ይህን ጸጋ ሲያጣ ከማንም ጋር መግባባት አይችልም። የሰው ልጅ ባሕርይ እንኳን ሰው ግሩማን የሚሆኑ የሚያስፈሩትን አራዊትን ማግራት መግዛት ብሎም አብሮ መኖር ያስችለዋል። ይህንን የቅድስና ጸጋችንን ያኔ በገነት ጸጋችን ሲገፈፍ ጥለነው ስለመጣን ዛሬ በራሳችን መልካም ባልሆነ ባሕርይ ተጠቅተን ተሰቃይተን ሰውንም ስናሰቃይ እንታያለን። እግዚአብሔር ለእኛ ለሰው ልጆች ‹‹ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ›› ብሎ የቅድስና ባሕርይን እንድንላበስ አክብሮ ሰጥቶናል። / ዘሌ 19÷2/

ከልጅነታን የሚዋረሰን ዓይነ ጥላ ለወደፊት ተንኮሉ እንዲመቸው ከልጅነታን የጭቅጭቅ፣የጠብ፣የኩርፊያ፣የእልከኝነት፣የእንቢተኝነት፣የአልሸነፍ ባይነት፣እኔ ያልኩት ካልሆነ በማለት የራሱን የጠባይ መገለጫ ውስጣችን በማስረጽ ነውጠኛ ሰው ያደርገናል። እነዚህን ያልተወደዱ ባሕርይ ይዘን እናድግና ከፍ ስንል ለራሳችን የራሳችን ባሕርይ ግራ እስኪገባን ድረስ ከሰው ጋራ ጥሩ ተግባቦት እናጣለን። ለዚህም ነው አንዳንዶቻችን ጥሩ መንፈሳዊ ሰው ለመሆን እንፈልግና መንፈሳዊ ጠባይ ግን አይኖረንም።

ዓይነ ጥላው በስውር የራሱን የክፋት ባሕርያት በእኛ ውስጥ ያሳድጋል። ቤተሰቦቻችን ‹‹ጠባዩ ነው፣እሱ/እሷ ከልጅነት ኃይለኛ ነው/ናት›› እያሉ ስለተስማሙ ለባሕርያችን እውቅና እየሰጡን እናድጋለን። እራሳችንን ችለን ከሰዎች ጋር፣ከጓደኛና ከቤተሰቦቻችን ጋር በፍጹም መግባባት አንችልም። የእኛ በሚመስል ግን በዓይነ ጥላው ባሕርይ ሰም ይሰጠናል።

ሁለተኛው ድንገት የባሕርይ ለውጥ እናመጣለን። ሳናውቀው የኃይለኝነት፣የቁጣና እኔ ያልኩት ወደሚል አደገኛ የባሕርይ ጥንውት ውስጥ እንገባለን። ከዛማ በሆነው ባልሆነው መቆጣት፣መነጫነጭ የዘወትር ሥራችን ይሆናል።

ይህ የባሕርይ አስከፊ ገጽታችን ወደ እኛ የሚመጡትን መልካም ነገሮችን ያሳጣናል። ዓይነ ጥላው እኛ ላይ ቁጭ ብሎ በቁጣ መንፈስ፣ማሕበራዊ ተግባቦታችንን ማቃወስ ይጀምራል። የሚያሳዝነው ዓይነ ጥላው ሰዎች የተናገሩንን መልካም ነገሮች ገልብጦ በማሰማት፣በሌላ አቅጣጫ በመተርጎም ለጠብ ይጋብዘናል። ለዚህም ነው አንዳንዶቹ ‹‹አንቺ ነገር ማጣመም ነው የምትችይው›› የሚባሉት።

እጮኛሞችን ደግሞ ገና በጓደኝነት ጊዜያቸው ከሁለት አንዱ ላይ ያለው ዓይነ ጥላ በቃላት፣በንግግር፣በፍላጎት፣በምርጫ እንዳይግባቡ እንዳይስማሙ ያደርጋቸዋል። ይህ አለመግባባት እየዋለ ሲያድር ብሎም ሲከር በቀላሉ ያለማንም ግን በዓይነ ጥላው ጣልቃ ገብነት መለያየት ውስጥ ይገባሉ። እየተዋደዱ፣እየተላመዱ በባሕርይ በሚመስል አለመግባባት ስንቱ ለመለያየት በቅቷል። የስንቱ የእጮኝነት ሕይወት በዓይነ ጥላ ስውር ደባ ፍቅር አልባ ሆኖ ተቀጭቷል።

የሚያሳዝነው በእጮኝነት ጊዜ የሚፈጠረው አለመግባባት፣ጭቅጭቅ ለሁለቱም ልክ እና አሳመኝ የሆነ ምክንያት አድርጎ ያሳያቸዋል። ታረቁ ሲባሉ እንቢኝ አሻፈረኝ ይላሉ። እጮኛሞችን ዓይነ ጥላው ማለያየት ሲፈልግ ከሁለት አንዱን ድንገት ባሕሪውን ይቀይራል። ያልተለመደና አዲስ የሚመስሉ ነገሮችን ያሳያል። በዚህን ጊዜ መደባበር፣መናናቅ፣መቀዛቀዝ መበሃላቸው ይፈጠርና ወደ ሌላ የጥርጥር ድምዳሜ ውስጥ ከትዋቸው ይለያያቸዋል።

የሚዋደዱ የሚፋቀሩ እጮኛሞች ለሰው ግራ እስኪሆን ድረስ ለምን እንደማይግባቡ፣ለምን እንደሚጨቃጨቁ አይውቁም። በተለይ ዛሬ ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን ብለው ከተቀጣጠሩ በመሃል ድንገተኛ አለመግባባት ይፈጠርና ተጨቃጭቀው ይለያያሉ። ነገሩ ካለፈ በኃላ ነው ከሁለት አንዳቸው ጥፋታቸው የሚታያቸው። ዓይነ ጥላው የልቡን ካደረሰ